ጥር 19 ቀን 2004 ዓ.ም

# <u>እግዝአብሔርን በገንዘብ የሚያገለገል፡ ብዙ ከተከፈለው ድያብሎስንም ያገለግላል !</u>

**ከአያልነሽ**

ሰሞኑን በበረከት እና በመንግስቱ ኃ/ማርያም መፅሐፍ አሳበው ተችዎች በመምሰል ነገር ግን ድብቅ ማንነታቸውን ያጋለጡ ግለሰቦች ከየስርቻው ብቅ፣ ብቅ ማለት ጀምረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ድብቅ ማንነታቸውን የተከላከሉ መስሏቸው በባለቤትነት (Coppy Rights) ሽፋን ለጥቁር (ናዚዎች) ጥብቅና የቆሙ ምሁሮች አልታጡም።

አንዳንዶች ደግሞ ቀድሞውንም ሡብዕናቸውን አውርደው ሕሊናቸውን የሸጡ ናቸውና **«የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም»** በሚል ለምንም የማይጨነቁ፤ ምንም ከማድረግም ወደኋላ የማይመለሱና ዘወትር ባልተረጋጋ ህሊና ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። እንደነዚህ ዓይነት ነውረኞችን ያገሬ ሰው **«ዓይናቸውን በጨው ያጠቡ»** ብሎ በዓይነ ቁራኛ የሚከታተላቸው ናቸው።

አንዳንዶች ደግሞ ድሮ ድሮ **«ኢህአፓ»** ነበርን፤ ከጀግንነቱም ጎራ ቢሆን ግንባር ቀደም ሆነን በወጣትነታችን የተሰለፍን ነበርን ይሉና አሁን ግን ከእኛ በኋላ **«ትግል ቆሟል»፤ «ኢሕአፓ የሚባል ነገር- የለም»፤ «ህዝብ ተሸንፏል»፤** ብለው ተኝተው በሕልማቸው የሚቃዡትን በቀንም ቆመው ያንባርቁታል።

አንዳንዶቹ ደግሞ ኢሕአፓ በዞረበት ያልዞሩ፤ በነበረበት ያልነበሩ ድንገት ግን ከሰማይ ዱብ ብለው፣ በፀረ ኢሕአፓነት ፅልመት ተጋርደው **ኢሕአፓ ሞቶ ተቀብሯል** ይሉና ሞቷል ባሉት ድርጅት ላይ ደግሞ መልሰው **«ሞት ለኢሕአፓ»** እያሉ ኡኡታቸውን ያቃልጡታል። ይህ ሁሉ ግን መነሻ አለው- ኩታን በየፈርጁ ነውና ሁሉንም በመልክ በመልካቸው መፈተሽ አግባብነት አለው።።

ከዚያ በፊት ግን ለአንባቢ ወገኖቼ ልብ እንድትሉት የምሻው አንድ ቁም ነገር አለ። ይኸውም በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን እያጠፋና ህዝቧንም ቁም ስቅል እያሳዬ የሚገኘውና ሥልጣን ላይ ያለው፣ ወያኔ እንጅ ኢሕአፓ አይደለም። ይሄ አንድ እውነት ነው። ይሁንና ለእነኝህ ወገኖች ግን ሌሊትም ሆነ ቀን እንቅልፍ የሚነሳቸውና የሲቃ ቅዠት የሚያስቃዣቸው **«ሞቶ ተቀብሯል»** የሚሉት ኢሕአፓ ነው። ለምን?

እስቲ በእነዚህኞች **«ኢሕአፓ ነበርን»** በሚሉት ሰዎች ልጀምር። እነኝህ ኢሕአፓ ነበርን የሚሉ ግለሰቦች (በእርግጥም ኢሕአፓ ከነበሩ) በኢሕአፓ ላይ እንዲህ ዓይነት የመረረ ጥላቻና ፀረ ኢህሕአፓ ዘመቻ ሲያካሂዱ ዝም ብለው ነው ማለት አይቻለም። ከጣራ በላይ የሚያስተጋቡት ጩኸታቸው በከባድ የህሊና ቁሰል የሚሰቃዩ ለመሆናቸው ያሳብቅባቸዋልና ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ እነኝህ ሰዎች ይሄን ያህል መሪር የሆነ ዘመቻ በኢሕአፓ ላይ ሲያወርዱ፣ አንድም ኢሕአፓን ከደው ለመንግስቱ ኃ/ማርያም ታማኝነታቸውን በማሳየት **«ማሪኝ አብዮቴ»** ብለው በቀድሞ ጓዶቻቸው ላይ የዘመቱና እያደኑ ወይም እየጠቆሙ ለነብሰ በላው ደርግ ለዕርድ ያቀረቡ፣ አለያም አንዳንዶቹ ደግሞ እነኛ **«ጓዶቻችን ናቸው»** ሲሏቸው የነበሩትን ራሳቸው ቆመው በዘይት ሲያስጠበሱም የነበሩ ላለመሆናቸው ማረጋገጫ የለም።

አንድ የማንክደው ሐቅ ግን ያኔ፣ ያኔ ኢሕአፓን በመከዳት የኢሕአፓ መዋቅርን ሲያስመቱና ጓዶችንም እያስለቀሙ ሲያስፈጁ የነበሩትን፣ በባዕድ አገር ያሉትንም ሆነ፣ በአገር ቤት (በወያኔ ሽፋን) የሚኖሩትን ሁሉ እናውቃለን! ልብ አድርጉ ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ (በ1983 ዓ.ም) የወያኔው የቀትር ጥላ ተብሎ ስም የተሰጠው ኢሕዴን (ኢሕአፓ) ነኝ እያለ ያወናብድ ነበርና ይሄንን የቀይ ሽበር ጉዳይ ትያትር ሊሰራበት ሞክሮ ነበር። በእርገጥ በቀይ ሽበር ልጆቻቸው የተፈጁባቸው እናቶች፣ አባቶች እህቶች፣ በአጠቃላይ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ማለት ይቻላል እውነተኛው ኢሕአፓና እውነተኛ ፍትህ የሚያገኝ መስሎት የልጆቹን ገዳዮች ሊፋረድ ያደረገውን መረባረብ ላስተዋለ፣ ፍትህ ምንጊዜም ቢሆን

በማዳፈንና በማድበስበስ ዳዋ ውጧት የማትቀር እንደሆን አማላካች ነው። ይህ የወያኔ ትያትር ሲካያሄድ እንደአጋጣሚ እኔም እዚያው ሆኜ ይሄን ሁሉ ትንግረት ተከታትያለሁናም ነው።
አንባቢዎች እባካችሁ ! ይሄንን ከዚህ በታች ያለውን ወደቦታው አድራሽ (ሊንክ) ተጭናችሁ (ክሊክ) በማድረግ ትመለከቱት ዘንድ ስጠይቅ ከታላቅ አክብሮት ጋር ነው።
http://www.youtube.com/watch?v=UIVUGnuCr9w&feature=player_embedded#

በእኛ በኩል በወደቀ ዛፍ ላይ ምሣር ማንሳት አስፈላጊ አይደለም ከሚል ችላ ብለንና ትኩረታችንን በሙሉ፣ አሁን ሕዝባችንን ቀስፎ ከያዘው ወያኔ ማላቀቅ ላይ ለማድረግ እንጅ፣ እንኳንስ የትናንቱን የደርግ/ኢሠፓ ዝቃጭ ታሪክ ቀርቶ የቅርቡን ማለትም ወያኔ ወደ አዲስ አበባ ሲገሠግስ መንገድ እየመሩ፣ ኢሕአፓ ነን እያሉ (ከደርግ/ኢሠፓ የጅምላ ጭፍጨፋና ግድያ የተረፉ) የኢሕአፓን ልጆች መልሰው በማስለቀም ለወያኔ ግብር ያቀረቡና የተሾሙ እንዳሉም እናውቃለን። አልፎ ተርፎም ተሾምን ብለው እያሳደዱ መግቢያና መውጫ ሲያሳጡ የነበሩ ሰዎችን ሙሉ ስምና ዝርዝር ከታሪካቸውን ጋር አስፈላጊ ከሆነ ማስቀመጥ ይቻላል።

እርግጥ ነው እነ በረከት ስሞዖንም እኮ በአንድ ወቅት ለአጭር ጊዜ ኢሕአፓ ውስጥ የነበሩ ናቸው - ግን ኢሕፓን ከደው ለወያኔ በማደር ዛሬ የሚያደርጉትን በማድረግ ላይ የሚገኙ የዛሬ ወያኔዎች ናቸው። እነኝህ ሰዎች ኢሕአፓን ከለቀቁበት ቀን ጀምሮ ወያኔ እንጅ ኢሕአፓ ሊሆኑ አይችሉም፤ አይደሉምም። ግን ያልሆነን ሆነ የወደቀን ተሠበረ ብለው የሚያስወሩት አንድም የደደቢቱ ተምች፣ አሊያም የባህረ ነጋሹ ሲያል ነው። ደግሞ እኮ እንዲህ ካላደርጉ እንዴት ሥልጣናቸውን ማስጠበቅ ይቻላቸዋል ?
መቼም ኢሕአፓና ወያኔ፣ ኢሕአፓና ሻዕቢያ ፍቅረኛሞች ናቸው ተብለው ለሃሜት የሚበቃ እውነት ማግኘት አይቻልም። ወጣም ወረደ ኢሕአፓ ደግሞ እነኝህን ጥንድ ጅቦች መታገሉን አላቆመም፣ አያቆምምም። ስለዚህ የእነርሱ ዝላይ መልሶ ራሳቸውን አውርዶ ያፈርጣቸው እንደሆን እንጅ  ለኢሕአፓ አይሞቀውም አይቀዝቅዘው። እንዲያው ለነገሩ ጨዋታውን ካመጣነው አይቀር ለመሆኑ በኢሕአፓ የትገል ታሪክ ውስጥ ኢሕአፓነት ያልነካው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ይገኛልን ?

የዛሬዋ ባህረነጋሽ/ኤርትራ እንኳ ልጆቿ በኢሕአፓ ታቅፈውና ተሰልፈው ለመሠዋታቸው፣ እነ ገለብ ዳፍላ (እሽቴን) እንደምሳሌ መጥቀሱ በቂ ምስክር ነው። ገለብ ዳፍላ (እሽቴ) የተሰዋው በ1982 ዓ.ም (ኢትዮ.አቆጣ) በሳንቂሳ (ቋራ) በተባለችው ወረዳ ከወያኔ ጋር በተደረገው ከባድ ጦርነት ነው። ገለብ ዳፍላ ኤርትራ ተወልዶ ያደገ፣ ኢሕአፓ ከመመሥረቱ በፊትና ከተመሠረተም በኋላ በኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ፤ ደርግ/ኢሠፓን፣ ሻዕቢያንና ወያኔን ታግሎ በማታገል መስዋዕት የከፈለ ዕንቁ ጓዳችን ነው። በረከት ስሞዖን ደግሞ ኢሕአፓን ከድቶ ለወያኔ በማደር የወንድሙን ሬሳ በጥርሱ አንስቶ የተረማመደ የኤርትራ ተወላጅ ነው።

ሐገርን ለማዳንና የሃገር ባለቤት ለመሆን የሚደረግ ትገል እኮ የውጭ-ነብስ ግቢ-ነብስ ግብግብ እንጅ የራት ግብዣ አይደለም። የጀመረ ሁሉ አብሮ ይዘልቃል ማለትም አይቻልም። የትግል ከባዱና ውስብስብነት መገለጫውም ደግሞ ይሄ ነው። ሌሎችም የበረከት ዓይነት ጉዶች በሽ ናቸው - ትገል አይደል እንዴ !። በትገል ውስጥ ክህደትን ሊያስቆም የሚችል ኃይል የለም። ያለው ምርጫ ሁለት ብቻ ነው። ለሀገር/ለሕዝብ አርበኛ ሆኖ መስዋዕት ሆኖ ማለፍ ወይም ደግሞ ከሃዲ ሆኖ የውሻ ሞት መሞት አለቀ። በዚህ መኃል ልላ የሥርጥ መንገድ የለም። በተረፈ ለድል አንድ ቀን ሲቀርም ቢሆን ከሃዲ ይኖራል - ይህ ያለ ሐቅ ነው።

አንዳንዶችም በኢሕአፓ ውስጥ ለአጭር ጊዜ አልፈው ወጣን ባሉ ማግሥት መፅሐፍ ፃፍን አሉና በኢሕአፓ አባልነታቸው የተገደሉ፣ ኢሕአፓ በመሆናቸው ብቻ የተጋዙና መስዋዕት የሆኑ ጓዶችን (ለእነርሱ ደግሞ ከአብራካቸው የተፈጠሩ የሥጋ እህትና ወንድሞቻቸው የሆኑትን) ታሪክ፣  **ለነብሰ ገዳዮቻቸው** ማስታወሻ ይሁንልን ብለው ገፀ-በረከት ማቅረባቸውን ተመልክተናል።  ይሁንና ለዚህ ሁሉ የህሊና ሠቀቀናቸው  ተጠያቂው፣ የየራሳቸው ህሊና እንጅ ኢሕአፓ ሊሆን ከቶ አይችልም።

ሌላው ደግሞ በቅርቡ አንድ የፖለቲካ ሳይንስ አስተማሪ ነኝ የሚሉ ሰው (**Copyrights & copy crimes**) በሚል ርዕስ ሥር አስገራሚ የሆነ ፅሁፍ በድረ-ገፅ ላይ ለቀው አስነብበውናል። የፅሁፋቸው መነሻ የመንግስቱ ኃ/ማርያም መፅሐፍ ያለአግባባ ተነበበ ብለው ለ**CopyRights** ጠበቃ የቆሙ መስለው የራሳቸውን ማንነት አጋልጠዋል።

እኝህ ሰው ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ ያሉት ከ1997 ዓ.ም (2005) ምርጫ በኋላ ይሁን እንጅ ራሳቸውን ወደ መደርከ አደባባይ ሲያቀርቡ ባዶ እጃውን አልነበረም ብቅ ያሉት- HR 2003 የሚል ነገር በእጃቸው ጨብጠው ነው ። ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች እንደሚባለው መሆኑ ነው። የፖለቲካ አቋማቸው ምን እንደሆን ባይታወቅም **«የሠብዓዊ መብት አክቲቪስት »** ናቸው ተብሎም በደጋፊዎቻቸው ይተረክላቸዋል - የሠበዓዊ መብት አክትቪስት ! ግሩም ነው። ወፍ እንደ አገሩ ይጮኃል ነው ነገሩ።

<u>**አውዛጋቢው ጉዳይ**</u> (ባይሆን ጥሩ ነበር)

በCopyrights ሽፋን መፅሐፉን አትሞ ለመንግስቱ ኃ/ማሪያም ገቢ ማስገባት የሚለውን እንኳን ወደጎን አድርገን፤ ቅንጣት ያህል ላፈሰሰው ደም፣ ላጠፋው ሕይወት ያልተጸጸተን ፋሽስት፣ በመብት ስም የሞራል ድጋፍ ለመስጠት መነሳት ራሱ ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ብቻ ሳይሆን፣ የእነኝህን ግለሰቦች ማንነትና የእስከአሁኑንም ጉዞዋቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳዬ እንቅስቃሴ ነው። በአንፃሩም የሥነ ልቡና ጠገጋቸውንም እንዲሁ። ስለዚህ አሁን በሚያደርጉትና በሚያሳዩን አካሄድ ስለ አገራችንና ስለ ነገው የሕዝባችን እጣ ፋንታ ብንጨነቅና መደረግ ያለበትን ብናደረግ፣ የዜግነታችን መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታችንም በመሆኑ ጭምር ነው። አገራችን ኢትዮጵያ እንደገና በሚያደሚትና በሚገድሏት ሰዎች እጅ ከወደቀች ትልቅ አደጋና የታሪክም ስህተት ነው ብለን ስለምናምን፣ በሕዝባችን ኪሣራ ምንም ዓይነት ነገር ልናስተናግድ አይጠበቅብንም፣ አይፈቀድልንምም፣ ማንም ደግሞ ሊፈቀድለት አይገባም። በቃ ማለት ዜግነታዊ ግዴታችን ነው። የኢትዮጵያዊው ሁሉም ኃላፊነትና ግዴታ ነው።

በነገራችን ላይ የናዚው ሂትለር የፕሮፓጋንዳ ሰው ዶክተር ጎብልስም እኮ በጣም የተማረና ምጡቅ የተባለለት ሰው ነበር። ግን እስቲ አሁን ማን ይሙት ጤነኛ የሆነ ሰው በመንግሥቱ፣ በዜናዊ ፣ በኢሳያስ፣ በጋዳፊ ይቀናል ? አንዳንድ ሰዎቻችን ግን ልክ እነርሱ የሆኑትን ለመሆን ያቀበቀቡና አሰፍስፈው ሲሟሟቱ የምናዩውም በዚህ ምክንያት ነው።

በጠንካራ ኢኮኖሚዋ የምትታወቀዋ ጀርመን ከዛሬ 70 ዓመት በፊት ናዚ ሂትለር በፈጃቸውና በአደረሰው እልቂት ሰበብ ጀርመን ውስጥ ሂትለር የሚባል ስም መጠቀም እንዳይቻል በህግ ተደንግጓል። ሂትለር በፈፀመው አስቃቂ ጭፍጨፋ ጀርመን እስከአሁን ደረስ እየከፈለች ነው። ይህ ብቻ አይደለም - ጀርመኖች ይህ ታሪክና የሂትለር ነገር ሲነሳ ሁልጊዜ የሚያፍሩበትና የሚሸማቀቁበት የታሪካቸው ህፀፅ ነው።

ሌላም ልጨምር። በአሳለፍነው የፈረንጆች 2011 ዓ.ም በአንድ ወጣት ኖርዌጃን የተፈፀመ አሰቃቂ ግድያ የበርካታ ኖርዌጃንን ህይወት ቀጥፏል። ይህ ድርጊት የዓለምን ህዝብ ያስደነገጠ ነበር። ግድያውን የፈፅመው ኖርዌጂያዊም በቁጥጥር ስር ይውልና በአጭር ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት ጉዳዩ መታዬት ይጀምራል። ይህ ወጣት ድርጊቱን ለምን እንደፈፀመ (ዕምነቱን፣ ራዕዩን) በቴሌብዥን ለማቅረብ እንዲችል በጠበቃው በኩል ይጠይቃል። ዳኞችም ወዲያውኑ የሰጡት መልስ አይፈቀድም የሚል ነበር - ይሄንን መሣይ የጭካኔ ድርጊት በቴሌቭዥን የማስተላለፍ መብት የለም በማለት ነበር ጉዳዩን የዘጉት። ምናልባት የኛዎቹ የመብት ተከራካሪዎች **"አንቀጽ 19"ኝን** ጠቅሰው መብቱ ነውና መናገር አለበት ብለው ዴሞክራሲና ፍትህ ከተከበረባት ኖርዌይ ጋር ሙግት ይገጥሙ ነበር ማለት ነው ? ለፍትህና ለመብት ተከራካሪ ነን እያሉ **« ሲሸላለሙ »** የኖሩት ሰዎች ለማን መብት እንደሚከራከሩና ፍትህን ሲሳለቁበት መመልከት፣ የነገዋ ኢትዮጵያ የሚጠብቃት የፅልመት ግርዶሽ ምን

ይመስል እንደሆነ አመላካች ነው። <u>እግዚአብሔርን በገንዘብ ያገለገለ፣ ብዙ ገንዘብ ከተከፈለው ዲያቢሎስንም ያገለግላል</u> ያልኩት ለዚህ ነው።

ሌሎችም አሉ። በ1983 ዓ.ም ወያኔ ኢትዮጵያን ለማጥፋት በአደባባይ እየለፈፈ ሲመጣ፣ እንኳን ደህና መጣህ ብለው መንገድ በመምራት፣ መፅሐፍ በመፃፍ፣ የምንሊክ ሃውልት ይፍረስ ብለው ሠልፍ በመውጣት **«ቡርቃ ዝምታሽ ምንድን ነው ? ተነሽና ወንዝሺን በተቆራረጠ የሰው ሥጋ ሙይ እንጅ ፣ ውኃሽንም በሰዎች የደም ጎርፍ አቅልሚው »** ብለው በበረከት እየታዘዙ መጽሃፍ ሲፅፉ የነበሩ ሰዎች፤ ዛሬ ደግሞ ከፋሽስቱ መጽሐፍ ጋር ሽርጉድ ቢሉ ምን ያስገርማል ? ዳሩ ግን እንዲህ ዓይነት ሠብዕና የተላበሱ ሰዎች ሁሌም ያን የተዋረደ ሠብዕናቸውን የደበቁ መስሏቸው ቀድመው ጣራ እስኪቀደድ ቢጮሁ የፍርኃታቸው ውጤት ነው። ምነዋ የቡርቃ ዝምታ ባለቤት በ1983 ዓ.ም በአዲስ አበባ መኃል ከተማ (ከሠአት በኃላ 10 ሠዓት) ላይ ከመሥሪያ ቤቷ ደጃፍ ሻዓቢያ ጠልፎ ያስወሰዳትን የሳራ ተክሌን መዳራሻ አይናገር ? የህሊና ቁሰል መድኃኒት የለውም። በህሊና ቁስል የሚሰቃዩ ሰዎች መድኃኒቱ የሚገኘው በእጃቸው ነው። ለራሳቸው ሕሊና መድኃኒቱ ራሳቸው እንጅ ፣ ማንም ሊሆን አይችልም። በሰው ላይ ግፍ ሠርቶና በደል ፈፅሞ ከሰው ዕይታ፣ ከፍትህ ደጅ ለጊዜው መሸሸ ይቻል ይሆናል ከሕሊና ዳኝነት ግን ምንጊዜም ተደብቆ ሆነ ሸሽቶ መኖር አይቻልም።

ለመሆኑ ለመንግሥቱ ኃ/ማርያም « **የመፃፍ መብት** » የሚከራከሩት የሠብዓዊ መብት አክቲቪስት ነን ባዮች ፣ ስለእነ ፀጋዬ ደብተራው መታሠርና መዳረሻቸው እስከአሁን አለመታወቅ፣ አልሰሙ ይሆን ? **ሆድን በጎመን ቢደልሉት፤ ጉለበት በዳገት ይለግማል አሉ ።** ዓመት ያስቃል

**የህዝብ ትገል ያሸንፋል**
**የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ**
**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር**

**ቸር ይግጠመን።**

January 28/2012